42

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ
# የገንዘብ ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTER OF FINANCE

ቁጥር / Ref. No. 7/Z/1/2/189

ቀን / Date 1 3 መጋቢት 2013

**ዝርዝራቸው በአባሪ ለተመለከቱ የፌደራል ባለበጀት መ/ቤቶች**
**በያሉበት**

**ጉዳዩ:- ያለ አገልግሎት የተከማቹ የመንግስት ንብረቶችን አወጋገድ ይመለከታል**

የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች በመንግስት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 8 ፊደል ተራ /ሸ/ ድንጋጌ መሰረት በመስሪያ ቤታቸው ሥራ የሚገኙ አገልግሎት የማይሰጡ የመንግስት ንብረቶች በህጉ የተፈቀዱ የማስወገጃ ዘዴዎችን ተጠቅመው በወቅቱ እንዲወገድ ማድረግ እንዳለባቸው የተደነገገ ሲሆን በመንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ደግሞ የነጠላ ዋጋቸው እስከ ብር 1,000 /አንድ ሺህ ብር/፣ ጥቅል ዋጋቸው ደግሞ እስከ ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ የሆኑ ንብረቶች በሽያጭ ሊያስወግዱ እንደሚችሉ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

ይሁን እንጂ ከፍተኛ ወጪ የወጣባቸውና አገልግሎት የማይሰጡ ወይም ከጥቅም ውጭ የሆኑና በወቅቱ መወገድ ሲገባቸው በተለያዩ ምክንያቶች ያልተወገዱ ንብረቶች ክምችት ከፍተኛ መሆኑን የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ባከናወነው ተከታታይ የኦዲትና ሱፐርቪዥን ስራዎች ለመረዳት የተቻለ ሲሆን፣ ለዚህም የመንግስት መ/ቤቶች እንዲያስወግዱ በመመሪያው የተቀመጠላቸው የሚወገዱ ንብረቶች ግምታዊ የገንዘብ ጣሪያ አነስተኛ መሆን አንዱ ምክንያት በመሆኑ በመመሪያው አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተቀመጠው የነጠላ ዕቃ ግምታዊ ዋጋ እና የጥቅል ግምታዊ ዋጋ የገንዘብ ጣሪያ ላይ ማስተካከያ ማድረግ አስፈልጓል፡፡

በመሆኑም ያለአገልግሎት የተከማቹ የመንግስት ንብረቶችን ለማስወገድ፣ በቀጣይም የተቀላጠፈ የአወጋገድ/ሽያጭ ሥርዓት እንዲኖር ለማድረግ እንዲቻል፣ በመመሪያው የተቀመጡ ሌሎች የንብረት ማስወገጃ ዘዴዎችና አሰራሮች እንደተጠበቁ ሆኖ ይህ ደብዳቤ ወጪ ከተደረገበት ዕለት አንስቶ ግምታዊ የነጠላ ዋጋቸው እስከ ብር 5,000/አምስት ሺህ ብር/ የሆኑና በአንድ ጊዜ ለሽያጭ የሚቀርቡ ንብረቶች ግምታዊ ዋጋ እስከ 500,000 /አምስት መቶ ሺህ ብር/ ድረስ የሆኑ ንብረቶችን ሽያጭ ለመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት መላክ ሳያስፈልግ በመንግስት መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ውሳኔ በሽያጭ እንዲወገዱ

አህመድ ሺዴ
ሚኒስትር

ስልክ
251-11-155 24 00,22 66 98
251-11-155 00 81,83 86 89

የፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1905,1037
እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ

ፋክስ/Fax
251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38

MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet
mofed.gov.et

ውክልና የተሰጣችሁ መሆኑን፣ እንዲሁም በዚህ ዙሪያ ከዚህ ቀደም የተላለፉ ሰርኩላሮች በዚህ ሰርኩላር የተሻሩ መሆኑን እያሳወቅን፣ የህዝብ ሀብት የሆኑ የመንግስት ንብረቶች ለበለጠ ጉዳት እና ብክነት እንዳይጋለጡ አፈጻጸሙ ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስባለሁ።

ከሰላምታ ጋር

አህመድ ሺዴ
ሚኒስትር

<u>ግልባጭ</u>፡-

- ለመንግስታ ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ
- ለመንግስት ግዥና ንብረት ማስገወድ አገልገሎት
  <u>አዲስ አበባ</u>